# ዜና መጽሄት

ቅጽ 19 ቁጥር 04

ዜና መድን

# የኢትዮጵያ መድን ድርጅት የዋንጫ ተሸላሚ ሆነ




የሽልማቱ ሥነ ሥርዓት በከፊል

የኢ.መ.ድ ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ባዘጋጀው የዱላ ቅብብል ውድድር ላይ ተሳተፎ የዋንጫ ተሸላሚ ሆነ፤ ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ የ2011 ዓ.ም የዱላ ቅብብል ውድድር (2019 IFH Relay) ለ16ኛ ጊዜ "በትክክለኛ ቦታ ተጠንቅቀን በመሻገር ራሳችንን ከትራፊክ አደጋ እንጠብቅ" በሚል መሪ ቃል ባዘጋጀው ውድድር የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ሠራተኞችን ጨምሮ ሌሎች የውጪና የሀገር ውስጥ ተወዳዳሪዎች የተሳተፉበት ውድድር ግንቦት 18 ቀን 2011 ዓ.ም ተከናውኗል፡፡

የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ በሚያዘጋጀው የዱላ ቅብብል ውድድር ላይ ሠራተኞቹን በየዓመቱ የሚያሳትፍ ሲሆን ይህም ጤናቸውን ከመጠበቅ ባሻገር የድርጅቱን ስም በበጎ ጎን ለማስጠራት የራሱን ሚና እንደሚጫወት ይታወቃል፡፡ የዘንድሮ የዱላ ቅብብል ውድድር በአዲስ አበባ

የሚገኙ ከዋናው መስሪያ ቤት፣ ዲስትሪክቶችና ቅርንጫፎች የተውጣጡ ሠራተኞች በውድድሩ ላይ እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡

ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ የ2011 ዓ.ም የዱላ ቅብብል ውድድር (2019 IFH Relay) ለ16ኛ ጊዜ የተካሄደ ሲሆን የውድድር ቦታው ከደንበል ህንፃ ወደ መስቀል ፍላወር ሆቴል በሚወስደውመንገድ ላይ ሲሆን በአጠቃላይ ውድድሩ ስድስት ኪሎ ሜትር የሸፈነ መሆኑ ታውቋል፡፡የኢትዮጵያ መድን ድርጅት በሴትና በወንድ በሁለት ቡድኖች የተወከለ ሲሆን በወንዶች በባንክ እና ኢንሹራንስ ዘርፍ በተደረገው ውድድር አንደኛ በመውጣት የዋንጫ ተሸላሚ መሆን ችሏል፡፡

## *የኢትዮጵያ መድን ድርጅት 4ኛውን የሠራተኞች በዓል ቀን በድምቀት አከበረ*



**የበዓሉ ሥነ ሥርዓት በከፊል**

የኢትዮጵያ መድን ድርጅት 4ኛውን ዓመታዊ የሠራተኞች ቀን በዓል (employees' day) በአዲስ አበባ ደረጃ ሰኔ 8 ቀን 2011 ዓ.ም አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ በሚገኘው መድህን ዲኮር አዳራሽ ውስጥ እንዲሁም ከአዲስ አበባ ውጪ ባሉ ዲስትሪክቶችና በስራቸው በሚገኙ ቅርንጫፎች ሰኔ 9 ቀን 2011 ዓ.ም በደማቅ ሥነ ሥርዓት አከበረ፡፡

በአዲስ አበባ ደረጃ የተከበረውን በዓል በንግግር የከፈቱት የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ነፃነት ለሜሳ ሲሆኑ በንግግራቸው አንጋፋውና አስተማማኙ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት በሀገሪቱ ለ43 ዓመታት ያህል የመድን ኢንዱስትሪውን ሲመራ የቆየና በመምራት ላይ ያለ ድርጅት ከመሆኑም በላይ በልማት ሥራዎች ላይ የበኩሉን አስተዋፅዖ እያበረከተ እንደሚገኝ ገልፀው

በዘንድሮው ዓመት በጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር አብይ አህመድ ሽገርን ለማስዋብ በታለመው ፕሮጀክት የቀረበውን የድጋፍ ጥሪ የድርጅቱ ሥራ አመራር ቦርድ በሰጠው ትኩረት ከፍተኛ ድጋፍ በማድረግ ላይ እንደሚገኝ አስታውቀዋል አክለውም እነዚህን ሁሉ ፕሮጀክቶች ማስቀጠል የሚቻለው እና ድርጅቱም እንደ ድርጅት መቀጠል የሚችለው በሀገራችን ሠላም በሁሉም አቅጣጫ ሲኖር ብቻ መሆኑን ጠቅሰው ሁላችንም እርስ በእርሳችን ከመተጋገዝ ባሻገር የተጀመረውን የሠላም እንቅስቃሴ በመደገፍ እንደቀድሞው ሁሉ ከቤት ብሎም ከጎረቤት እንዲሁም በአቅራቢያችን ካሉት ማህበረሰቦች ጋር በያለንበት ሠላምን በማጠናከር በፍቅር በመኖር የበኩላችንን ድርሻ እንድንወጣ አሳስበዋል፡፡




የኢ.መ.ድ ዋና ሥራ አስፈፃሚ የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር ሲያደርጉ

በሌላ በኩል ደግሞ የድርጅቱ ዕድገት ከጊዜ ወደ ጊዜ ከፍ እያለ እንደመጣ እና በአሁኑ ሰዓት ጠቅላላ ሀብቱ ከ7 ቢሊዮን ብር በላይ መድረሱን እንዲሁም የቅርንጫፍ ስርጭቱና ተደራሽነቱ እየጨመረ መጥቶ አሁን ዋና መ/ቤትን ጨምሮ በሀገሪቱ 102 ቅርንጫፎችንና አገናኝ ቢሮዎች ተከፍተው አገልግሎት በመስጠት ላይ እንደሚገኙ ገልፀው ድርጅቱ የሠው ኃይሉን ለማዘመን (Deloeit Consultancy) በተሰኘ ዓለም አቀፍ አማካሪ ድርጅት አማካይነት ረዘም ያለ ጊዜ የወሰደ የሰው ኃይል ልማት ጥናት በማስጠናት ለተፈፃሚነቱ ጅማሮ ላይ መድረሱን አሳውቀዋል፡፡ በማያያዝም ድርጅቱ ከዚህ በፊት ቃል የገባቸውና ከሠራተኛው መሠረታዊ ፍላጎቶች ማሟያ ውስጥ የቤትና የመኪና መግዢያ ብድር ሲሆን አፈፃፀሙ ላይ በገጠመው ተግዳሮት የዘገየ ቢሆንም ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጋር ውይይቶችን በማድረግ ባንኩ በስሩ ለሚሰሩ ሠራተኞች ከሚሰጠው የብድር አገልግሎት ጋር ተመጣጣኝ በሆነ መንገድ ለመስጠት መስማማቱን በፅሁፍ ማረጋገጫ ከመስጠቱም በላይ የመግባቢያ ሰነድ (MOU) ለመፈራረም በድርጅቱ የህግ አገልግሎት

ዳሬክቶሬት በኩል እየታየ መሆኑንና በጥቂት ሳምንታት ውስጥ ተጠናቆ አገልግሎቱን መጠቀም እንደሚጀመር በመግለፅ ንግግራቸውን አጠቃለዋል፡፡

በመቀጠልም የኢ.መ.ድ ሠራተኛ ማህበር ፕሬዘዳንት የሆኑት አቶ ደስታ በርኸ ንግግር ያደረጉ ሲሆን በንግግራቸው ሠራተኛው ሲኖር ድርጅቱ እንዲሁም ድርጅቱ ሲኖር ሠራተኛው እንደሚኖር ጠቅሰው ለድርጅቱ ብልፅግና እያንዳንዱ ሠራተኛ እጅ ለእጅ ተያይዞ ቃል የሚገባበት ቀን መሆኑን አሳውቀዋል፡፡

የኢ.መ.ድ ሠራተኞች ይበልጥ እንዲተጉ ድርጅቱ በየዓመቱ ከሚያስመዘግበው ትርፍ ቢያንስ ለሠራተኞቹ 1% (አንድ ፐርሰንት) እንዲሰጥ ለበላይ አመራሮች አሳስበው ድርጅቱ ይህንን የሚያደርግ ከሆነ በስሩ የሚገኙ ሠራተኞች ደግሞ 10 እጥፍ አድርጎ ለመመለስ ዝግጁ እንደሆኑ ገልፀው ንግግራቸውን አጠቃለዋል፡፡



የኢ.መ..ድ ሠራተኛ ማህበር ፕሬዘዳንት አቶ ደስታ በርኸ ንግግር ሲያደርጉ

በሌላ በኩል ደግሞ ከኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ተወክለው የመጡ አካላት መልዕክት ያስተላለፉ ሲሆን በንግግራቸው ክብደቱ ከ45 ኪ.ግ በላይ እና እድሜው ደግሞ 18 እስከ 65 ድረስ የሆነ ማንኛውም ሰው ደም በመለገስ የወገኑን ህይወት እንዲታደግ ጥሪ አስተላልፈዋል፡፡ በተጨማሪም የቀይ መስቀል አባል በመሆን ቀይ መስቀል ይዞት የተነሳውን ሰብዓዊ ተግባር ሠራተኛው እንዲደግፍ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

በበዓሉ ላይ የድርጅቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ነፃነት ለሜሳ እና ከፍተኛ የማኔጅመንት አባላት የኬክ መቁረስ ሥነ ሥርዓት አከናውነዋል፡፡



የኢ.መ.ድ ማኔጅመንት አባላት የኬክ መቁረስ ሥነ ሥርዓት ሲያከናውኑ

በመጨረሻም የሠራተኞች ቀን በዓልን ምክንያት በማድረግ በሠራተኞች መካከል ሲከናወኑ በነበሩ ስፖርታዊ ውድድሮች ላይ ለተሳተፉ የምስክር ወረቀት የመስጠት ሥነ ሥርዓት ተከናውኗል፡፡ በወንዶች የእግር ኳስ ወድድር ሪከቨሪ የቴክኒክ ማዕከል 1ኛ የወጣ ሲሆን ማዕከላዊ አዲስ ዲስትሪክትና ዋና መ/ቤት 2ኛ እና 3ኛ በመውጣት የምስክር ወረቀት ወስደዋል፤ በሴቶች እግር ኳስ ደግሞ 1ኛ ምዕራብ አዲስ ዲስትሪክት 2ኛ ዋና መ/ቤት በመውጣት የምስክር ወረቀት ከዋና ሥራ አስፈፃሚ እጅ ተቀብለዋል፡፡ በሌላ ውድድር ደግሞ ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ባዘጋጀው የዱላ ቅብብል ወድድር ላይ ድርጅቱን በመወከል በባንክና ኢንሹራንስ ዘርፍ 1ኛ በመውጣት የዋንጫ ተሸላሚ በመሆን የድርጅቱን ስም በበጎ ያስጠሩ ተወዳዳሪዎች የተገኘውን ዋንጫ ለዋና ሥራ አስፈፃሚ በእለቱ በመገኘት አስረክበዋል፡፡

## የተሠጡ ስልጠናዎች

- እ.ኤ.አ. ከሚያዚያ 15 — 19, 2019 ለ6 ሠራተኞች በ "Marine Cargo Insurance" ላይ፣
- እ.ኤ.አ. ከግንቦት 6 —10, 2019 ለ14 ሠራተኞች በ "Property &Pecuniary Insurance" ላይ፣
- እ.ኤ.አ. ከግንቦት 13 — 17, 2019 ለ15 ሠራተኞች በ "Principle & Practice of Insurance" ላይ፣
- እ.ኤ.አ. ከሰኔ 10—14, 2019 ለ8 ሠራኞች በ "Contractors & Engineering Insurance" ላይ፣
- እ.ኤ.አ. ከሰኔ 10 — 14, 2019 ለ7 ሠራኞች በ "Motor Insurance" ላይ በአጠቃላይ ለ50 ሠራተኞች ስልጠናዎች ተሰጥተዋል።

## ሠራተኛ ነክ ዜናዎች

## አዲስ የተቀጠሩ ሠራተኞች!

ጣይቱ ጌታነህ
ጽዳት/ተላላኪ
ወልድያ ቅርንጫፍ
እ.ኤ.አ ሚያዝያ 3 ቀን 2019

ዘላለም ሲሳይ
ሹፌር
ገለምሶ ቅርንጫፍ
እ.ኤ.አ ሚያዝያ 3 ቀን 2019



ደስታ ለሜሳ
ሴክሬታሪ/ካሸር
ሻምቡ ቅርንጫፍ
እ.ኤ.አ ሚያዚያ 5 ቀን 2019



ደራራ ካባ
ጥበቃ
ሻምቡ ቅርንጫፍ
እ.ኤ.አ ሚያዝያ 5 ቀን 2019

ነቾ ዋቅወያ
ጥበቃ
ሻምቡ ቅርንጫፍ
እ.ኤ.አ ሚያዝያ 5 ቀን 2019

ረቢቱ ፈይሳ
ጽዳት/ተላላኪ
ሻምቡ ቅርንጫፍ
እ.ኤ.አ ሚያዝያ 5 ቀን 2019



ዳኛቸው አበበ
ጥበቃ
ባኮ ሳተላይት ቢሮ
እ.ኤ.አ ሚያዝያ 11 ቀን 2019



መልካሙ ኦብሳ
ጥበቃ
ባኮ ሳተላይት ቢሮ
እ.ኤ.አ ሚያዝያ 11 ቀን 2019

ገልቹ ወተቻ
ጥበቃ
ቡሌሆራ ቅርንጫፍ
እ.ኤ.አ ሚያዝያ 25 ቀን 2019

አዱላ ሙማ
ጥበቃ
ቡሌሆራ ቅርንጫፍ
እ.ኤ.አ ሚያዝያ 25 ቀን 2019

ጃርሶ ሜኢሳ
ጥበቃ
ቡሌሆራ ቅርንጫፍ
እ.ኤ.አ ሚያዝያ 25 ቀን 2019


ኢብራሂም ከማል
ሰልጣኝ ኦፊሰር
በደሌ ቅርንጫፍ
እ.ኤ.አ ሚያዝያ 25 ቀን 2019

በሽር አሚዶ
ሰልጣኝ ኦፊሰር
በደሌ ቅርንጫፍ
እ.ኤ.አ ሚያዝያ 25 ቀን 2019



ቤተልሔም ለገሰ
ሴክሬታሪ/ካሽር
በደሌ ቅርንጫፍ
እ.ኤ.አ ሚያዝያ 25 ቀን 2019

ኤደን ጫላ
ካሽር
ባቱ ቅርንጫፍ
እ.ኤ.አ ግንቦት 6 ቀን 2019



ራህዋ በላይ
ሴክሬታሪ/ካሽር
መቀሌ ሳተላይት ቢሮ
እ.ኤ.አ ግንቦት 9 ቀን 2019



ደሳለኝ ሀምቢሳ
ሰልጣኝ ኦፊሰር
በደሌ ቅርንጫፍ
እ.ኤ.አ ግንቦት 13 ቀን 2019



ገነት ታደሰ
ተላላኪ
ዋ/መ/ቤት
እ.ኤ.አ ግንቦት 13 ቀን 2019

ታረቀኝ ሳሙኤል
ሰልጣኝ ኦፊሰር
ሀዋሳ ህይወት ቅርንጫፍ
እ.ኤ.አ ግንቦት 21 ቀን 2019

ንብረት ዳመነ
ሴክሬታሪ/ካሸር
በቆጂ ሳተላይት ቢሮ
እ.ኤ.አ ግንቦት 29 ቀን 2019

ሰንዴይ ጋትካች
ሰልጣኝ ኦፊሰር
ጋምቤላ ቅርንጫፍ
እ.ኤ.አ ሰኔ 6 ቀን 2019



እመቤት በቀለ
ጽዳት/ተላላኪ
ኮምቦልቻ ቅርንጫፍ
እ.ኤ.አ ሰኔ 10 ቀን 2019



ሰላማዊት ስጦታው
ጽዳት
ጎንደር ቅርንጫፍ
እ.ኤ.አ ሰኔ 12 ቀን 2019

አጥሬ ቀልቤሳ
ተላላኪ
ዋ/መ/ቤት
እ.ኤ.አ ሰኔ 17 ቀን 2019

ጽዮን ገ/እግዚአብሔር
ተላላኪ
ማዕከላዊ አዲስ ዲስትሪክት
እ.ኤ.አ ሰኔ 17 ቀን 2019



መርጋ ታከለ
ሰልጣኝ ኦፊሰር
ጊምቢ ቅርንጫፍ
እ.ኤ.አ ሰኔ 19 ቀን 2019

ስመኝ ዘለቀ
ተላላኪ
ህይወት አዲስ ዲስትሪክት
እ.ኤ.አ ሰኔ 24 ቀን 2019



ኢትዮጵያ ታደሰ
ጽዳት/ተላላኪ
ባህር ሳተላይት ቢሮ
እ.ኤ.አ ሰኔ 27 ቀን 2019



ሀየሎም ብርሃኑ
ሴክሬታሪ/ካሸር
ማይጨው ሳተላይት ቢሮ
እ.ኤ.አ ሰኔ 27 ቀን 2019

**የኢንተግሬትድ ኮሚዩኒኬሽን ቡድን ወደ ድርጅታችን ለተቀላቀላችሁ ሠራተኞች መልካም የስራ ዘመን እንዲሆንላችሁ ይመኛል!!!**

# በጡረታ የተሰናበቱ

አልጋነሽ ዩሐንስ
ካሸር
አዳማ ህይወት ቅርንጫፍ
እ.ኤ.አ ግንቦት 9 ቀን 2019

አዘነጋሽ ዩሐንስ
ኦፐሬሽን ኦፊሰር
ሰሜን አዲስ ዲስትሪክት
እ.ኤ.አ ግንቦት 9 ቀን 2019

ስመኝ ምዕራፍ
ፕሪንሲፓል ኦዲተር
ዋና መ/ቤት
እ.ኤ.አ ግንቦት 9 ቀን 2019

ብርቱካን አኖሬ
ተላላኪ
ሐዋሳ ዲስትሪክት
እ.ኤ.አ ግንቦት 9 ቀን 2019

- የኢንተግሬትድ ኮሚዩኒኬሽን ቡድን በጡረታ ለተሰናበታችሁ ሠራተኞች መልካም የእረፍት ጊዜ እንዲሆንላችሁ ልባዊ ምኞቱን ይገልፃል!!!

# ከዚህ አለም በሞት የተለዩ ሠራተኞች

ግርማ ኪዳነማርያም
የመኪና ተረካቢና አስረካቢ
ዋና መ/ቤት
እ.ኤ.አ ግንቦት 26 ቀን 2019

ሙሉጌታ አይናለም
ማርኬቲንግ ኦፊሰር
ጋምቤላ ቅርንጫፍ
እ.ኤ.አ ሰኔ 5 ቀን 2019

- የኢንተግሬትድ ኮሚዩኒኬሽን ቡድን ከዚህ አለም በሞት ለተለዩ ሠራተኞች ለነብሳቸው እረፍትን ይመኛል!!!

**የኢትዮጵያ መድን ድርጅት የዜና መድን መጽሔት ስላነበባችሁ ከልብ እያመሰገን ስለ መጽሔቱም ሆነ በአጠቃላይ ስለ ድርጅቱ ያላችሁን አስተያየት በድርጅቱ የኢ-ሜይል አድራሻ bdrm@eic-et.com በፖስታ ሣ.ቁ. 2545 ለኢንተግሬትድ ኮሚዩኒኬሽን ቡድን በሚል እንድትልኩልን በአክብሮት እንጠይቃለን፡፡**